መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም

# ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው ማን ነው? "ኢሕአዴግ" የሚባለውስ እውን ለኢትዮጵያ "የእድገት ግንባር' ነውን? እነሆ! ጥያቄዎቼን ለገብሩ አስራትና ሸሪኮቻቸው በድጋሚ

ከ ኢያልነሽ

የወያኔ/ህወሓት መሥራች የነበሩት ገብሩ አሥራት ዛሬም "አረና ትግራይ" የሚባል የጎጥ ድርጅት መሥራች በመሆን፣ ድርጅት ነው ያሉትን ይህንን ተውሳክ ለማስተዋወቅ ከአዲስ አበባ አውሮጳና አሜሪካ ለመወናጨፍና ለመጓጓዝ ብዙ አልተቸገሩም። እነሆ! ዛሬም ወደ አሜሪካ በመምጣት ይህ አዲስ የጎጥ ተቋም ያለበትንና የደረሰበትን "ዕደገት" ለደጋፊዎቻቸው ለማስረዳት ብቅ ብለዋል።

ገብሩ አሥራት የወያኔ/ህወሓት መሥራችና መሪ ሆነው በቆዩበት ድርጅት ውስጥ ዛሬ ቢባረሩም ከ30 ዓመት በላይ በፍርሃት ሸብበው ሲያዝዟቸውና እንዳሻቸው ሲያደርጓቸው የነበረውን የድርጅታቸው ተከታይ የነበረ/የነበሩ ግለሰብ/ቦችን በማፈላለግ፣ ዛሬም ድጋፋቸውን "ለዓረና ትግራይ" እንዲያደርጉላቸው በመባዘን ላይ ናቸው። ገብሩ አሥራት እነኝህን የእኔ ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች ሲያፈላልጉ እንደለመዱት በቀዳማይ ድርጅታቸው ሕወሓት/ወያኔ እንዳሰለፏቸው ሁሉ፣ አሁንም ከተቻለ የ"አረና ትግራይ" አባል እንዲሆን/እንድትሆን ለማግባባትም ጭምር ነው። የቀድሞዎቹ ወያኔዎች የዛሬዎቹ አረናዎች እነኝህን ማገርና ምሰሶ ሆነው ለወያኔ ተሰልፈው የገበሩ የትግራይ ልጆችን ዛሬም ይጠቀሙባቸው ዘንድ በመወትወት ላይ ይገኛሉ።

ደግ። የእነ ገብሩና ሰዬ ዓላማ ምንድን ነው? ከአዲስ አበባ ወደ አውሮጳና አሜሪካስ ለመመላለስ እንዴት ቀለላቸው? የዚህ ሁሉ ዋና ግብስ ምንድን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እኛ ኢትዮጵያዊያኖች ዛሬም ደግመን መፈተሹ ከኢትዮጵያ አንፃር ይጠቅመናልና በድጋሚ እንድናየው አሁንም አንባቢዎችን በትህትና እጠይቃለሁ። የገብሩ አስራት ሆነ ሰዬ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ የወያኔዎች ተልዕኮና ግዳጅ ገና አልተገባደድም። ስለሆነም እነሆ ከዛሬ 33 ዓመት ጀምሮ የወጠኑት የወያኔዎች ኢትዮጵያን የማጥፋት ተልዕኮ፣ በገጠማቸው የሥልጣን ሽኩቻ ግብግብ ሳቢያ ሳይፈጸም ቀርቷልና፣ አሁንም እየደከሙለት መሆኑ እየታየ ነው። ታዲያ የእነገብሩ አሥራት መኳተን የዚሁ ያልተገባደደው ኢትዮጵያን የማጥፋቱ ተልእኮ/ግዳጅ ቅጥያ ነው። ዓላማው ይህ ከሆነ ግቡ ደግሞ ያልቋጩት የእነ ሰዬ ሆነ የማንኛቸውም ወያኔዎች ፍላጎት "የትግራይ የበላይነት" አሁን ባለው መንገድ እንዲቀጥል፣ እጅግ ከሄደም ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ "የትግራይ ትግርኝ" መንግሥት ቆሞ የበላይነቱን ይዞ እንዲቀጥል ለማድርግ ያላቸውን ጽኑ ምኞት ያሳኩ ዘንድ፣ ገብሩ አሥራት የተኙ ካሉ ለመቀስቀስ፣ የራቁ ካሉ ለማቅረብ፣ እስከዛሬ በፍርኃት ተሸብበው

የሚኖሩትንም ገንዘብ በማጉረስ ከፍርኃቱ እንዲነቃቁ ለማድረግ ፣ በተደጋጋሚ እየተመላለሱ  ሰዎቻቸውን  አንድ እንዲሏቸው ተግተው በመሥራት ላይ ናቸው። እነ ሰዬ ውጭ ያሉ ሰዎቻቸውን በተመላለሱ ቁጥር በድብቅ  የሚሏቸው እንዲህ ነው። ከ30 ዓመት በላይ በእኛው ፍርኃት (እኛን በመፍራት) ብቻ ተኝተህ ከቀረህ/ሽ እኮ ይሏቸዋል፣ - እነኝህን የፍርሃታቸው ሰለባ የሆኑ ተከታዮቻቸውን በሚስጥራዊ ስብሰባቸው ላይ! - እኛን ፈርተህ ተኝተህ ከቀረህ/ሽ እኮ "የሚመጣው" ይሏቸውና የማስፈራሪያ  አርጩሜአቸውን እያወናጨፉ በፍርሃት የሚኖሩትን የትግራይ ልጆች ሊያነቃቁ/ሊቀሰቅሱ ነው ወደ ውጭ ምልልሱን የተያያዙት።

እርግጥ ነው፣ እነ ሰዬ  ይህንን የማስፈራሪያ አርጩሜያቸውን ሁሌ ከእነኝህ የማስፈራሪያቸው ሰለባ ከሆኑ የትግራይ ልጆች ፊት ላይ ሁሌ ቢያውዛውዙት፣ ከሺዎችች በላይ የትግራይ ልጆችን በሳህል/ኤርትራ ለኢሳያስ አፈወርቂ ጭዳ አድርገዋልና ቢፈሯቸው የሚጠበቅ ነው። በኢሳያሱና በእነ ሰዬው የስለላ መረብ፣ የትግራይ ልጆችን  ከሻዕቢያና ከወያኔ ጎን አልቆማችሁም ወይም አልተሰለፋችሁም በሚልም እትብታቸው በተቀበረበት ትግራይ ውስጥ ሳይቀር በእነሰዬ/ገብሩው ወያኔ እየታነቁ ተፈጅተዋልና፣ እነኝህ የሥነ ልቡና ተጠቂ የሆኑ የትግራይ ልጆች ዛሬም እነሰዬን እየፈሩ የመኖራቸው ሚስጥር ይኸው ነው። ለረጅም ጊዜም የሚቀጥል ይሆናል። ግን የትግራይ ልጆችን በተለይም ውጭ ያሉትን እስከመቼ አገር እየጠፋ ዝምታ አለ! መባሉ ግን ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን ናትና ጥያቄው ቢነሳ በየትኛውም ሚዛን ሊያስከፋቸው አይገባም ባይ ነኝ ። የሆኖ ሆኖ  አሁንም በውጭ የምትኖሩ የትግራይ ልጆች በእነ ሰዬና ገብሩ አሥራት በአጠቃላይ፣ በወያኔ/ህወኃት በተለይ የተጫነባችሁን የፍርሃት ሸምቀቆ በጥሳችሁ በመውጣት፣ ኢትዮጵያን በማዳኑ ተልእኮ ላይ ትረባረቡ ዘንድ ኢትዮጵያዊያኖች ሁሌ ለእናንተ ጥሪ ብናስተጋባ፣ ይመለከታችኋልም ከሚል ነው። ወገኖቼ! ኢትዮጵያ እየፈረሰች ትግራይ ብቻዋን ልትቆም አትችልምና ነው። ከኤርትራም፣ ከጎረቤታችን ሱማሌም ልንማርና ልትማሩ ይገባልና።  እነሰዬና እነ ገብሩ እናንተን ጭዳ አድርገውና አርግፈው ለኤርትራ ምን አስገኙተውላት? ብላችሁ መጠየቅም ይኖርባችኋል። ለእናንተስ ቢሆን ምን ተረፋችሁ? ኤርትራን ገንጥለው "አገር" አደረግን ያሉት እነሰዬ፣ ዛሬም ትግራይን ከሌላው ኢትዮጵያ ነጥለው "የትግራይ መንግስት" በድብቅ አቁመው እያለ፣ የዚህ የትግራይ ክፍለ ሀገር "የትግራይ መንግስት ፕሬዚዳንት በመባል ይጠሩ" የነበሩት ገብሩ አስራት፣ ዛሬ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፣ ስለ"ኢሕአዴግም" ማንነት  ሊሰብኩን የሞራል ብቃት አለኝ ብለው ሲነሱ ዛሬም የሚያዋርዱት፣ የናቁትና የሚንቁት እናተንና የተከበረውን የትግራይ ሕዝብ ነው እላችኋለሁ።
የተከበራችሁ አንበቢዎቼ ሆይ!
እነ አቶ ገብሩና ሰዬ አብርሃ አነሳሳቸው ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሆኖ እያለ "ኢትዮጵያ" እና "ኢህአዴግ" እያሉ ደጋግመው ሲያላዝኑ እውነት ከልባቸው ነውን? ብሎ መጠየቅ አግባብነት አለው። ለመሆኑ ስሙ እንዲህ የሚያማልለው "ኢሕአዴግ" የሚሉት ድርጅታቸው እውነት እንደስሙ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ

ግንባር" ያውም የኢትዮጵያ ነውን? ነበርስ? ከነበረና ካለስ ለኢትዮጵያ 17 ዓመት ይህ ተቋም ሚናው አዎንታዊ ነው ወይስ አሉታዊ ? እነ ገብሩ አሥራትን ኮትኩቶ ካሳደጋቸውና ካሳደጉት ከወያኔ/ህወኃት በላይ፣ መጤውን "ኢሕአዴግ" እንዲህ በፍቅር "ኢሕአዴግ ኢህአዴግ" በማለት ከአፋቸው አልነጥል ያሉት ከቶ ለምን ይሆን? ከወያኔ እና "ኢሕአዴግ" በአንጋፋነቱና በኃብቱስ የትኛው ይበልጣል? እነ ገብሩ አሥራትና ሸሪኮቻቸው ቅርበታቸውስ ለወያኔ ነው ወይስ ለኢሕአዴግ? ለመሆኑ እንዲህ "ገናና" ያደረጉት "ኢሕአዴግ" በእነ ገብሩ አሥራትና በእነ ስዬው አብርሃ መንደር ትግራይ ውስጥ አለ? እነ ገብሩስ ይሄንን "ገናና" ያደረጉትን ድርጅት "ኢሕአዴግን"፣ እስከዛሬ ለምን ይሆን በትግራይ ክ/ሀገር በእነርሱው "ክልል" አላስገባ ብለው ያቆሙት? ምን አጥፍቶ ይሆን? በእነ ገብሩና/ስዬው ወያኔ፣ ትግራይ ውስጥ እንዳይገባ የታገደው "ኢሕአዴግ" ለመላው ኢትዮጵያ የተሰጠውና ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የተደረገው "ወርቆቹ" የሠሩት በመሆኑ"ከወርቆቹ" የተሰጠን ስጦታ ይሆን? ወዘተ፣ ወዘተ ...እያልን እነኝህን መሰል ሚጢጢ ጥያቄዎች ቀርቶ ኢትዮጵያን እያናጋና እየናጠ ያለውን ከባድ ከባዱን የእነ ገብሩ አሥራትን ወያኔያዊ መርሃ ግብር መጠየቅ በተቻለ ነበር። ግን ለመጠየቁም ሆነ መልስ ለማግኘቱ ሁሌም <u>"መበደል መበደል ወታደር በድሏል ግን አርሶ አደር ይካስ"</u> በሚለው ቆፈን እንድንታሰር ያደርጉናልና መጠየቅ አልደፈርንም፣ አንደፍርምም ። የሚገርመው ግን ይህን እንድንለብሰው የተሰጠንን "መበደል መበደል" የሚል ቆፈን ዛሬ ዛሬ "ለገዥዎቻችን" ብቻ ሳይሆን የሚያገለግለው፣ ጊዜ እላይ ሰቅሎ አውርዶ ላፈረጣቸው ግፈኞችም ለእነስዬ አብርሃ፣ ለእነ ገብሩ አሥራትና መሰሎቻቸውም ጭምር እንድንጠቀምበት ተደንግጓልናል። ለመሆኑ ብጻይ ገብሩ! ይሄኛውስ አንቀጽ ስንት ይሆን?

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ዛሬ ከ17 ዓመት በኋላ ስለ "ኢሕአዴግ" ማንነት ለመጻፍ ስነሳ፣ እናንተን አንባቢዎቼን ሆነ ማንኛውንም ሰው ስለ "ኢሕአዴግ" ማንነትና ምንነት ኢያውቅም/ኢታውቁም ከሚል የተሳሳተ ግምት ተነስቼ ሳይሆን፣ ማንንም ምንም የማይፈሩ ግብዞች የብዙኃኑን ተመልካችና ታዛቢ አስተሳሰብና የማገናዘብ ችሎታን ከምንም ሳይቆጥሩ ንቀውና ደፍጥጠው ለማለፍ ብዙ ሲደክሙና ሲባዝኑ በማየቴ ነው። "ኢሕአዴግ" "ኢሕአዴግ" ኢሕአዴግ" !!! ።

"ያልወለድኩት ልጅ አባባ አባባ ሲለኝ፣ አፈን ዳባ ዳባ አለኝ" ይላሉ አበው። ግሩም አባባል ነው፣ ላስተዋለው። ዛሬ ኢሕአዴግ! ኢሕአዴግ! ኢሕአዴግ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! በእነ ገብሩ አሥራትና ስዬ አፍ ሲባልና ሲሉት ምን ያህል እንድሚከፋባቸውና ደም ደም እንደሚል የሚነግራቸው ባለመኖሩ እስካሁን አልተረዱትም። ቀድሞውንም "ኢሕአዴግ" ብለው የሰየሙት ይህ ተቋም፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የኢትዮጵያን ሕዝብ መቀመቅ ውስጥ ለመክተት የሳሉት ጎራዴ መሆኑን ለእነ ገብሩ አሥራት ሥውር ሆኖ እንደሆነ እንጅ ለመላው ኢትዮጵያ ወለል ብሎ የተገለጠ ነበር/ነውም። ይህ ብቻ አይደለም፤ "ኢሕአዴግ ኢሕአዴግ፣ ዘመነ-

*እንድግድግ" ተብሎም በመላ የኢትዮጵያ ህዝብ ደረጃ በ1997ዓ.ም ግንቦት ላይ የመጨረሻ ልኩን እንዲያውቅ፣ በአደባባይ በዓለም ፊት ተነገሮትም ነበር። ግን የእነ ስዩ ውልድ ነውና የሕዝብ ዓይን፣ የሕዝብ ቁጣ አልበገረውም፣ አልገረፈውም።*

*እነ ገብሩ አሥራትና ፍልፍሎቻቸው "ኢሕአዴግ ኢሕአዴግ" እያሉ 1000 ጊዜ ደጋግመው በመጥራት የሚያሞካሹቱ ድሪቷቸው፣ የወያኔ/ሕወሓትን የጥፋት ተልዕኮ የደበቀላቸው እየመሰላቸው ከአፋቸው አይነጥሉት እንጅ፣ አስተዋዩና አዋቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ገና ወያኔ እግሩ አዲስ አበባን ሲረግጥ ነበር፣ ሳይውል ሳያድር ባልተቋረጠ ሠላማዊ ሠልፍ አጋልጦ እዚያው ራስክን ቻል ብሎ የምገተው። አከታትሎም ይህንን የወያኔን ኮተት፣ <u>ተለጣፊ ነህ</u> ይህንን ያማረ ስም አጎናጽፎታል። በአጠቃላይ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ተቋም የወያኔ ጭንብል መሆኑ ተነቅቶበት 17 ዓመት ሙሉ እንደተጠላ ነበር የተንገታገተው። ግን "ለኢሕአዴጋዊያን" የተባለው ቢባል ጌጣቸው ነውና 17 ዓመት ሳይቆጠቁጣቸው፣ ሳያደማቸው ኖረዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ድሪቶ የተሸበለሉትንና የተጠቀለሉትን "ኢሕአዴጋዊያን" ማንነት ሲገልጥ ደግሞ፣ የወያኔ <u>የቀትር ጥላ</u> ብሏቸው ነበር፣ እነኝህን የ"ኢሕአዴግ" ቅቤ ጠባሾች። ለመሆኑ እነኝህ "ኢሕአዴጋዊያን" እነማን ናቸው? ኢሕአዴግ ራሱስ ምንድን ነው? የዚህ ድሪቶ ደራችና ማሐንዲስ/አባት ማን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ዓብይ ጉዳዮች በሚቀጥለው ጽሁፌ ይዠ እስክቀርብ ድረስ ወያኔዎች በአጠቃላይ፣ የዚህ ድርጅት መስራቾች በሙሉ በተለይ፣ ፀረ-ኢትዮጵያና ኢትዮጵያን ለማጥፋት የመጡና ብዙ የሄዱ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚጠሉ ናቸው ስንል ከመሬት ተነሥተን ሳይሆን በተግባራቸው ካሳዩን፣ የ33 ዓመት ገድላቸው በመነሣት ነው። እነኝህ ሰዎች ኢትዮጵያን ሊወርር ከመጣው ጣሊያን ጋር የሚያመሳስል መልካቸውን አቅርቤ ለዛሬው በዚህ ልሰናበታችሁ፡፡*
*ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር ባደረጉት ጥረት የኢትዮጵያን ሕዝብ እንድአሁኑ እንደ ወያኔ በዘር ነበር የሸነሸኑት። እጠቅሳለሁ፥*

*" ጣሊያኖች በዘርና በሃይማኖት ለመከፋፈል ባደረጉት ጥረት ሆን ብለው ኦሮሞን ከአማራ፣ እሥልምናን ከክርስትና አስበልጠው ይቀሰቅሱ ነበር። ይህም ህዝቡን በመለያየት በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት በመሆኑ፣ እሥላሞች መስጊድ እንዲሠሩና ወደ መካም እንዲሄዱ ያበረታቱ ነበር። በዚህም መሠረት ኤርትራና ሶማሊያን ጨምሮ በሥድስት ክ/ሀገር በመክፈል የምስራቅ አፍሪካ ኢጣሊያ ብለው ሰየሟት። የክፍፍሉም ክፍል ትግራይን ጨምሮ የኤርትራን ክፍል በአሥመራ ማዕከልነት፤ አማራን በጎንደር ማዕከልነት፤ ሸዋን በአዲስ አበባ ማዕከልነት፤ እንዲሁም ኦሮሞ-ሲዳሞን በጅማ ማዕከልነት፤ ኢደሬን በሐረር ማዕከልነት ሐረርጌ ክ/ሐገርን ጨምሮ ሶማሊያን አንድ ላይ በማድረግ ሸንሸኑት ይላል" የጥቅሱ መጨረሻ*

*ምንጭ፥ የደብተራው ድረ ገጽ (በኢጣሊያ ወረራ የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ ታሪክ ማስታወስሻ! ከብርሃኑ ተሰማ) ለመረጃው! አቶ ብርሃኑ ተሰማንና ደብተራውን አመሰግናለሁ"።*
*የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞ በሙሉ ይፈቱ!*
*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!*
*ቸር ይግጠመን!*

*ሴብተምበር 22 /2008*

EthioLion.Com